አንፃር እንዲህ ከማድረግ የተሻለ አማራጭ ያልነበረው መሆኑን ብናምንም ከትግላችን ዓላማና ለዚህ ዓላማ መሳካት ሕዝቡ ከከፈለው ከባድ መስዋዕትነት አንፃር ሲመዘን የዚህ የይቅርታ ጥያቄ እንደምታ ምንድነው የሚለው ጥያቄ ለታሪክ ፍርድ ትተነው እናልፋለን።

ይህ አመራር በቅርቡ ሕዝብንና መንግሥትን ይቅርታ ጠይቆ ከእስር ቤት ከተፈታ በኋላ በተለያዩ ቡድኖች ተከፋፍሎ ወደ እርስ በርስ መበላላት ተሸጋግሮ ይገኛል። ዛሬ ሁሉም እየተናገሩ ያሉት ትናንትና እንዲሳሳቱ ያደረጋቸውና ዛሬም መግባባትን የነሳቸው ችግር ገና ከጅምሩ የነበረ መሆኑን ነው። ኢዴአፓ-መድህን አቋም ወስዶ ከቅንጅቱ እራሱን እንዲለይ ያደረገው እና ባለፉት ሁለት ዓመታትም ሲናገር የነበረው ይህንን ችግር ነበር። ትናንትና ኢዴአፓ-መድህን በዚህ ችግር አስገዳጅነት ከቅንጅቱ መለየቱ ብቻ እንደ ክህደትና ከፍተኛ ጥፋት ተቆጥሮ ነበር። ዛሬስ በተከታታይ እየተፈጠረ ላለው መለያየትና መፈረካከስ ተጠያቂው ማነው?

ትናንትና የተመኙትና የተንሰፈሰፉለት ሥልጣን ከእጃቸው ሊገባ የተቃረበ ስለመሰላቸው ኢዴአፓ-መድህን ይህንን ሥልጣን ተጋርቶ ድርሻቸውን እንዳያሳንስባቸው ወይም ለዚህ ሥልጣን እንቅፋት እንዳይሆንባቸው በመስጋት ከመንገድ ሊያስወግዱት በቅንጅቱ ውስጥ ግንባር ፈጥረው በአንድነት የታገሉት የመኢአድና የቀስተዳመና መሪዎች ዛሬ ደግሞ እርስ በርሳቸው ለመጠፋፋት የሚወነጃጀሉ ባለአንጣዎች ሆነዋል። ገና ቅንጅቱ ሲመሰረት ኢዴአፓ-መድህን ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል የዲሞክራሲያዊነት ችግር ያለባቸው፣ ትግሉ በደረሰበት ደረጃና ቅንጅቱን ሊያጋጥሙ ከሚችሉ ፈተናዎች አንፃር ብቁ መሪ ሊሆኑ የማይችሉ መሆናቸውን አስረግጦ ተከራክሮ ነበር። ለቅንጅቱ ውድቀት አንዱ ምክንያት የሆነው ይህ ጉዳይ በተግባር መረጋገጡ  ዛሬ በገሃድ የታየ ቢሆንም በወቅቱ ፓርቲያችን ያቀረበውን መከራከሪያ ከሥልጣን ጥመኝነትና ካለማወቅ የመነጨ እንደሆነ አድርገው አጥብቀው የተከራከሩት ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ዛሬ ደርሰው ኢንጂነር ኃይሉ ሻውልን በብቃት ማነስና በአምባገነንነት ሲወነጅሉ እያየን ነው። ከዛሬ ሁለት አመት በፊት ኢዴአፓ-መድህን ከቅንጅቱ ተገፍቶ እንዲወጣ ሲደረግ የቅንጅቱ የትግል ዓላማና የሕዝቡ ምኞት በቅንጅቱ ውስጥ የቀስተዳመናው ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በፈጠሩት ገደብ የለሽ የሥልጣን ጥመኝነትና መርህ አልባነት የተነሳ መንገድ መሳቱን በድፍረት ገልፆ ነበር። ባለፉት ሁለት አመታት ይህ የኢዴአፓ-መድህን አቋም በፓርቲያችን የሥልጣን ጥመኝነትና ቅንጅቱን ለማፍረስ ከታለመ ሴራ የመነጨ ተደርጐ ሲቀሰቀስብን ነበር። ዛሬ የቅንጅቱ ሊቀመንበር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል ብቻ ሳይሆኑ የራሱ የቀስተዳመና መስራች የነበሩት ፕ/ር መስፍን ወልደማሪያም ጭምር ይህንን ለሕዝብ እያረጋገጡ ናቸው። ሁሉ ነገር ኢዴአፓ-መድህን ሲናገረው ስህተት፣ እነሱ ሲናገሩት ግን እውነት ይሆናል ተብሎ በግብዝነት ካልታሰበ በስተቀር የኢዴአፓ-መድህን ስህተት የት ላይ ነበር?

ባለፉት ሁለት ዓመታት አንዳንዶች ለቅንጅቱ መፍረስ የቅንጅቱ አመራር ከተከተለው የተሳሳተ የትግል ስልት በላይ ኢዴአፓ-መድህንን ሲወነጅሉ ቆይተዋል። ይህንን ሆን ተብሎ የተሰራጨ ውዥንብር እውነት አድርገው የተቀበሉ ብዙ ሰዎች መኖራቸው ግልፅ ነው። ይህንን  ውዥንብር እውነት አድርገው የተቀበሉትንና በዚህ ምክንያት ጭምር ኢዴአፓ-መድህንን ሲወነጅሉና ሲያጥላሉ የቆዩ ሰዎችን ዛሬ የምንጠይቃቸው ጥያቄዎች አሉን። ኢዴአፓ-መድህን ከቅንጅቱ ሲወጣ የተቀሩት ሦስት ፓርቲዎች ቅንጅት ሆነው እንዳይቀጥሉ ለማድረግ የኢዴአፓ-መድህን ከቅንጅቱ መውጣት ብቻውን በቂ ምክንያት ሊሆን ይችል ነበር? ለመሆኑ ቅንጅት ለመሆን አራት ፓርቲ መሆን የግድ ነውን? ለቅንጅቱ መከፋፈልና እርስ በርስ መበላላት ተጠያቂው ኢዴአፓ-መድህን ነው ከተባለ ኢዴአፓ-መድህን ከቅንጅቱ ከወጣ በኋላ ክፍፍሉ    በአገር ውስጥና በውጭ አገር ባሉ የቅንጅቱ ስብስቦች ብቻ ሳይሆን እስር ቤት በነበረው አመራር ውስጥም ጭምር ለምን ቀጠለ? ኢዴአፓ-መድህን ከቅንጅቱ ከወጣ በኋላ በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር ለነበሩ ማለቂያ ላልነበራቸው መከፋፈሎችም ጭምር ተጠያቂው ኢዴአፓ-መድህን ሊሆን ነውን? እስር ቤት የነበሩ የቅንጅት አመራሮች ከእስር ቤት ከወጡ በኋላ  ያጣላቸውና ዛሬ የዶ/ር ብርሃኑና የኢንጂነር ኃይሉ ቡድን ተብለው እንዲከፋፈሉ ያደረገው ኢዴአፓ-መድህን ነውን? ከእስር ቤት የወጡት የቅንጅት መሪዎች ሰሞኑን ከእነ አቶ ተመስገን ዘውዴ ጋር አብረው ለመስራት መወሰናቸውን ሰምተናል። ትናንት እነ አቶ ተመስገን ፓርላማ በመግባታቸውና በቅንጅት ስም አዲስ ፓርቲ በመመስረታቸው ምክኒያት እንደነ አቶ ልደቱ ከሃዲ ተብለው በእነዚህ የቅንጅት መሪዎች ሲወገዙ ነበር። ታዲያ ዛሬ ምን አዲስ ነገር  ተፈጥሮ ነው- ከሃዲ ብለው የፈረጁአቸውን ሰዎች ቢያንስ ይቅርታ ባልጠየቁበትና ፓርላማ መግባትን ትክክለኛ ውሳኔ አድርገው ማመናቸውን ባልገለፁበት ሁኔታ አብረው ለመስራት የወሰኑት? የፖለቲካ ሰዎቻችን እንዲህ ዓይነት የአቋም መዋዠቅ ውስጥ ሲገቡስ ለምን? ብሎ



☏ 0115-508727    0114655765    ✉ 101458
0115-508728